የሰ/መ/ቁ. 37741

ሰኔ 4 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ መኰንን ዘውዴ- ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ ተሾመ ሽፈራው- አልቀረቡም

2. ወ/ሮ ዘርፌ ኀባቸው- አልቀረቡም

3. አቶ ጌታቸው መንገሻ- ወራሽ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ይህ ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በደራ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ ሦስተኛ ተጠሪ በገንዘብ እዳ ምክንያት አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎችን በደራ ወረዳ ፍ/ቤት ከሰው ካስፈረዱ በኂላ ንብረትነቱ የፍርድ ባለእዳዎቹ /የአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች/ የሆነ ቤት በፍርድ አፈፃፀም ተሸጦ እዳው እንዲከፈል ተብሎ የአፈፃፀም ትእዛዝ ተሰጥቶ ይሄው ቤት ለአመልካች ተሸጦ እዳው እንደተከፈለ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ከዚህ በኂላም የፍርድ ባለእዳዎች የይግባኝ ቅሬታ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ይግባኝ ባዮች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለመ/ሰጭ /ለስር ከሳሹ/ ይክፈሉ ተብሎ የተሰጠውን ዋናውን ውሳኔ በመሻር በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡ ከዚህ ውሳኔ በኂላም ፍርዱን ያስፈጸመው የወረዳ ፍ/ቤት ዋናው ውሳኔ የተሻረ መሆኑን መሰረት በማድረግ የተሸጠውን ቤት ተከሳሾች እንዲረከቡት በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህንኑ ቤት በፍርድ አፈፃፀም በኩል በተደረገ ሽያጭ ገዝቼዋለሁ የሚሉት የአሁን አመልካች ይህንኑ የወረዳውን ፍ/ቤት ትእዛዝ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ትእዛዝ ጉድለት የሌለው ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

ከዚህም በመቀጠል የይግባኝ ቅሬታቸውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ዋናው ውሳኔ ከተሻረ ተከራካሪ ወገኖች ቀድሞ ወደ ነበሩበት ሁኔታ ለመመለስ ጥያቄ ካቀረቡ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 349/1/ መሰረት ወደነበሩበት እንዲመለሱ መደረግ አለበት፤ ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ተሸጧል የተባለው ቤት ለስር ተከሳሾች እንዲመለስ ሲታዘዝ የሽያጩን ገንዘብ የስር ከሳሽ እንዲመልሱ መደረግ ሲገባው ይህ ያልተከናወነ ስለሆነ በዚሁ መሰረት የሽያጩን ገንዘብ የስር ከሳሹ ለአመልካች እንዲመልሱ በማለት የስር ፍ/ቤትን ትእዛዝ በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት ወሳኔውን አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት እንደዚሁም የስር ከሳሹ በተጠሪነት ተጣምረው ባለመገኘታቸው እሳቸውን ሦስተኛ ተጠሪ በማድረግ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤታታውም እንደሚከተው ተመርምሯል፡፡

በአንድ ፍ/ቤት የተሰጠ ፍርድ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተለወጠ ወይም የተሻሻለ እንደሆነ ማናቸውም ተከራካሪ ወገን ነገሩን በመጀመሪያ ለተመለከተው ፍ/ቤት ሲያመለከት የተወሰደው ገንዘብ ወይም ንብረት እንዲመለስ ተስማሚ መስሎ የታየውን ትእዛዝ መስጠት እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 349/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ንብረትነቱ የአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች የሆነው ቤት በፍርድ አፈፃፀም ለአሁን አመልካች ተሸጦ የሽያጩም ገንዘብ የፍርድ ባለመብት ለነበሩት ለአሁን ሦስተኛ ተጠሪ ተከፍሏል፡፡ የአሁን አመልካችም ይህንኑ በፍርድ አፈፃፀም በሽያጭ ያገኙትን ቤት አሳልፈው ለሌላ ወገን መሸጣቸውን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የስነ-ስርአት ሕጉ ድንጋጌ መሰረት ፍርዱ በይግባኝ በተለወጠ ጊዜ በዚሁ መሰረት ተከራካሪ ወገኖች ፍርዱ ከመፈጸሙ በፊት ወደነበሩበት እንዲመለሱ ትእዛዝ መስጠት የሚቻል ሲሆን ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ቤቱ በፍርድ አፈጻጸም ለአመልካች ከተሸጠ በቤቱ ላይም ለውጥ ከተደረገበት በኂላ እንደገና ለሌላ ወገን የተሸጠ ስለሆነ በዚህ ሁኔታ ቤቱ ለስር ተከሳሾች /ለአሁን አንደኛ ተጠሪዎች/ ይመለስ መባሉ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ የድንጋጌውም ይዘት ሲታይ ፍ/ቤቱ ሁኔታዎችን በማገናዘብ ተገቢ መስሎ የታየውን ትእዛዝ መስጠት እንደሚችል የሚያሳይ ፈቃጅ ድንጋጌ እንጂ አስገዳጅ ድንጋጌ አይደለም፡፡

ስለሆነም ከፍ ብሎ በተጠቀሰው አኳኋን ግራ ቀኙ ወደነበሩበት ሊመለሱ ይገባል ተብሎ እስከ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 48176 በ4/9/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 42032 በ17/5/99 የሰጠው ውሳኔ፣የሰሜን ሸዋ ዞን ከ/ፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11335 በ28/9/98 የሰጠው ትእዛዝ እንደዚሁም የደራ ወረዳ ፍ/ቤት በ24/8/98 የሰጠው ትእዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በፍርድ አፈፃፀም የገዙትን ቤት ለአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች ሊመልሱ አይገባም ብለናል፡፡
3. የቤቱን የሐራጅ ሽያጭ ገንዘብ የስር የፍርድ ባለመብት የነበሩት የአሁን ሦስተኛ ተጠሪ አቶ ጌታቸው መንገሻ ለአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች ሊመልሱ ይገባል ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
5. በዚህ ችሎት ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸም ግልባጩ ለደራ ወረዳ ፍ/ቤት ይተላለፍ ብለናል፡፡
6. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ